ባለረዥም ፀጉር ሁኖ ቀያይ መስመር ያለበትን ጥቁር አለባሽ ልብስ የሚያምርበት ከአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) የበለጠ እጅግ ውብ ሰው አልተመለከትኩም።

ከበራእ- አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፦ "ባለረዥም ፀጉር ሁኖ ቀያይ መስመር ያለበትን
ጥቁር አለባሽ ልብስ የሚያምርበት ከአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) የበለጠ እጅግ ውብ ሰው አልተመለከትኩም። ፀጉራቸው ትከሻቸውን ይመታ ነበር። በሁለቱ ትከሻዎቻቸው መካከል መራራቅ አለ። ረጅምም አጭርም አይደሉም።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

በራእ ቢን ዓዚብ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ከአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) የበለጠ ከርዝመቱ የተነሳ ፀጉሩ ትከሻው ድረስ የደረሰና ቀያይ መስመሮች ያሉበት ጥቋቁር ሽርጥና ኩታ የለበሰ አንድም እጅግ ውብ ሰው አልተመከትኩም ብለው ተናገሩ። በተጨማሪም ከርሳቸው አካላዊ ተፈጥሮ መካከል በሁለቱ ትከሻዎቻቸው መካከል መራራቅ እንዳለ፣ ደረታቸው ሰፊና ቁመታቸው አጭርም ረጅምም ሳይሆን መካከለኛ ቁመት እንደሆነ ተናገሩ።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/2990